# በካሊፎርኒያ የ2020 ጠቅላላ ምርጫ ላይ ድምፅ የሚሰጡበት መንገድ

ASIAN AMERICANS ADVANCING JUSTICE ASIAN LAW CAUCUS

## ይዘጋጁ

**በምርጫው ድምፅ ለመስጠት ቀደም ሲል ተመዝግበው ከሆነ፣** ወደ voterstatus.sos.ca.gov በመሄድ የሰፈሩትን የእርስዎ መረጃወች ትክክለኛነት ያረጋግጡ። የፖስታ አድራሻዎን፣ የኢሜይል አድራሻዎን ያጣሩ፣ የተተረጎሙ የምርጫ ሰነዶች እንዲደርሱዎት የሚፈልጉ መሆኑንም ይጠቁሙ።

**ካልተመዘገቡ፣** በኦንላይን registertovote.ca.gov መመዝገብ ይችላሉ ወይንም ወደ DMV፣ ፖስታ ቤት፣ ቤተ መጻሕፍት ወይንም ወደ ካውንቲዎ የምርጫ ጽ/ቤት በመሄድ ቅጽ መቀበልና መሙላት ይችላሉ። ቀነ ገደቡ ካለፈብዎትም የምርጫ ቀንን ጨምሮ እስከ ምርጫው ቀን ባሉት ቀናት ውስጥ መመዝገብ ይችላሉ።

## ከቤትዎ ሆነው ድምፅ መስጠት

እስከ ኦክቶበር 19 ድረስ ከተመዘገቡ፣ የድምፅ መስጫ ሰነድ በመልእክት መቀበያ አድራሻዎ (**በፖስታ ቤት**) ይላክልዎታል።



የድምፅ መስጫ ወረቀቱን ሞልተው፣ ፊርማና ቀን ካሰፈሩበት በኋላ ከመላክዎ በፊት አሺገው በፖስታ ቤት መላክ ይችላሉ።



ፖስታውን ለመላክ ቴምብር አያስፈልግም! **ፖስታው እስከ ኖቬምበር 3** ድረስ ቴምብር የተከፈለበት መሆኑን ያረጋግጡ::

## በአካል ድምፅ መስጠት

የምርጫው ቀን **ማክሰኞ፣ ኖቬምበር 3/2020** ነው። የምርጫ ጣቢያዎች ከጥዋቱ 7 a.m. **እስከ ምሽቱ 8 p.m ክፍት ሆነው ይቆያሉ።** በአካባቢዎ ያለውን የድምፅ መስጫ ጣቢያ ለማወቅ ይኽንን አስፈንጣሪ ይጫኑ፡ sos.ca.gov/elections/polling-place

**አብዛኞቹ ካውንቲዎችም ከቅዳሜ፣ ኦክቶበር 31/2020 ጀምሮ በአካል ድምፅ የመስጠት ዕድል ይሰጣሉ፤** አንዳንዶቹም ከዚህ ቀን አስቀድመው በአካል ድምፅ መስጠትን ያስጀምራሉ። በአካባቢዎ ከሚገኝ የምርጫ ጽ/ቤት ጋር ይነጋገሩ። አስቀድሞ ድምፅ የሚሰጥባቸውን ቦታዎች እና የመቀበያ ሳጥኖችን አድራሻ እዚህ አስፈንጣሪ ላይ ማየት ይችላሉ፡ caearlyvoting.sos.ca.gov



በካውንቲዎ የምርጫ ጽ/ቤት ወይም የትኛውም የምርጫ ጣቢያ ወይንም የድምፅ መስጫ ማዕከል የምርጫ ፖስታዎን

ማስገባት ይችላሉ። አብዛኞወቹ ካውንቲዎች ከኦክቶበር መግቢያ ጀምሮ ዝግጁ የሚደረጉ ደህንነታቸው የተጠበቀ የድምፅ መስጫ ሳጥኖች ይኖራቸዋል።

ሒደቱን በተቻለ መጠን ቀላል ለማድረግ፣ የድምፅ መስጫ ወረቀት በመልእክት መቀበያ አድራሻዎ (በፖስታ ቤት) በኩል ከተላከልዎት በአካል ድምፅ ለመስጠት ይዘውት ለመምጣት ይሞክሩ።

55 Columbus Avenue, San Francisco, CA 94111 | T (415) 896-1701 | www.advancingjustice-alc.org